የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት
ETHIOPIAN ARTIFICIAL INTELLIGENCE INSTITUTE

# ዲጂታል ኤ.አይ

ቅፅ 01 ቁ 06 የካቲት 2018 ዓ.ም



ኤ.አይ ለሁሉም!
AII4ALL!

AI CREATVE AWARD

CREATE COMPETE WIN

# የAI ሙዚቃ ውድድር

በኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት እና በእሁድ ኤ.አይ ስቱዲዮ በጋራ ትብብር የተዘጋጀ ነው። ዓላማውም የሀገራችንን የጀግንነት ታሪክ በተለይም የአድዋን ድል በዘመናዊ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ቴክኖሎጂ ታግዞ ለመዘከር እና የኢትዮጵያን የፈጠራ ኢንዱስትሪ ወደ አዲስ የቴክኖሎጂ ምዕራፍ ማሸጋገር ነው።




## የውድድሩ ቅድመ ሁኔታዎች

1. **የድምጽ ፋይል፡** ጥራቱን የጠበቀ የMP3 ወይም WAV ፎርማት።
2. **የርዝመት ገደብ፡** ሙዚቃው ከ2 እስከ 5 ደቂቃ ርዝመት ያለው መሆን አለበት።
3. **የተወዳዳሪ መረጃ፡** ሙሉ ህጋዊ ስም፣ የሚሰራ ስልክ ቁጥር እና የኢሜል አድራሻ።

**ማሳሰቢያ፡** የEAII እና የEhud AI ማህበራዊ ሚዲያ ገጾችን ፎሎው ማድረግ ግዴታ ነው።

## ጠቅላላ ሽልማት




**1,000,000 ብር**

**የማስረከቢያ የመጨረሻ ቀን**
**መጋቢት 7**

ለማስረከብ ይህን ይጠቀሙ
**www.creativeaward.ai**

**Create • Compete • Win**



# ማውጫ


ወቅታዊ ኤ.አይ ዜና . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 01
አርቲፊሻል ኢንተለጀንስን በነጻ የት እንማር? . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 07
ኢትዮጵያ የአፍሪካ የቴክኖሎጂ አቅጣጫ አመላካች . . . . . . . . . . . . . . . . 08
ኤ.አይ እና የግብርናው አብዮት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 10
EFPAPP የዲጂታል ዘመኑ ፖሊስ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 12
የአይን ህመምን በሞባይል ስልክ የሚለየው . . . . . . . . . . . . . . . . . . 14
የኢንስቲትዩቱ ዲጂታል ቤተ-መጽሐፍት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 16
ኤ.አይ እና ፖሊሲ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 19
እንግዳችን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 21
ከኤ.አይ ስታርታፕ ማዕከል እስከ ዓለማቀፋዊ ተፅዕኖ . . . . . . . . . . . . . 24
የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ መጽሐፍት ጥቆማ . . . . . . . . . . . . . . . . . . 25
አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ እንወቅ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 26
ከጎብኚዎች አንደበት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 27
ወሩን በፎቶ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 28
ኢንስቲትዩቱን ይጠይቁ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 32

# ራዕይ

ኢትዮጵያ በ2022 ዓ.ም
በአፍሪካ በአርቲፊሻል
ኢንተለጀንስ ቴክኖሎጂ
ግንባር ቀደም የሚያደርጋትን
ተቋም ዕውን ሆኖ ማየት

# ተልዕኮ

ሀገራዊ እውቅና ያለው
የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ተቋም
በመገንባት በዳታ ላይ የተመሰረተ
የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ
ሥርዓቶችን በመጠቀም ሀገራዊ
ችግሮችን ለመፍታት፤
ውጤታማነት እና ምርታማነትን
የማሳደግ አቅም ማጎልበት

ኤ.አዩ ዲጂታል
ቅፅ 01 ቁ 04 ታህሳስ 2017

# ወቅታዊ ኤ.አዩ ዜና




## ኢትዮጵያ በዓለም ሁለተኛውን የኤ.አዩ ዩኒቨርሲተ መገንባት ጀመረች

በዓለም ሁለተኛዉ የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ በኢትዮጵያ መጀመሩን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ( ዶ/ ር) ገለፁ።

ኢትዮጵያ በወርኃ የካቲት የ39ኛዉን አፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ በስኬት አከናዉናለች። በዚህ አህጉራዊ ጉባኤ የኢ. ፌ. ዴ. ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ( ዶ/ ር) ባደረጉት ንግግር አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ አንዱ የንግግራቸው ትኩረት ነበር።



ጠቅላይ ሚኒስትሩ በንግግራቸው እ. ኤ. አ 2020 ላይ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ፈር ቀዳጅ የሆነውን የኤ. አይ ኢንስቲትዩት ማቋቋሟን አስታዉሰዋል። የዚህ መሰረት ፍሬ የሆነዉና በዓለም ሁለተኛዉ የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ መጀመሩን በንግግራቸው ገልጸዋል።

ይህ የኤ. አይ ዩኒቨርሲቲ በአፍሪካ ፈር ቀዳጅ ከመሆን ባለፈ ለመጪዉ ትዉልድ ምቹ የሆነ የዘርፉን ሥነ- ምህዳር ለመፍጠር ያስችላል ተብሏል።

# የዓለማችን ሁለተኛው የኤ.አይ ዩኒቨርሲቲ

የኢ. ፌ. ዴ. ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በ6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 10ኛ መደበኛ ስብሰባ የመንግሥት የ6 ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ከምክር ቤት አባላት ለሚነሱ ጥያቄዎች ዝርዝር ምላሽ እና ማብራሪያ አቅርበዋል።



" ኢትዮጵያ በዓለማችን ሁለተኛ የሆነውን የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ዩኒቨርሲቲ በመገንባት ላይ ትገኛለች።

ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)
የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር

ቴክኖሎጂን አስመልክቶ በሀገሪቱ እየተሰሩ ስለሚገኙ ስራዎች ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ መንግሥት ከያዛቸው አምስቱ የእድገት ምሠሦዎች አንዱ ቴክኖሎጂ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ከዓመታት በፊት የኤ. አይ ኢንስቲትዩትን ስታቋቁም አንድም የአፍሪካ ሀገር በተቋም ደረጃ የመሰረተ አለመኖሩን በመግለጽ፥ አሁን ደግሞ በዓለማችን ሁለተኛ የሆነውን የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ውስጥ በመገንባት ላይ እንድሚገኝ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስታውቀዋል። በወራት ውስጥ ስራ ይጀመራል የተባለው የኤ. አይ ዩኒቨርሲቲ በአፍሪካ ፈር ቀዳጅ ከመሆን ባለፈ ለመጪዉ ትዉልድ ምቹ የሆነ ሥነ- ምህዳር ለመፍጠር ያስችላል ተብሏል። ለዚህም አስቻይ የሆኑ ቅድመ ዝግጅቶች ሲደረጉ መቆየታቸው ተጠቁሟል።



በዚህም የሚኒስትሮች ምክር ቤት በ53ኛ መደበኛ ስብሰባው መደመር የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ዩኒቨርሲቲን በአዋጅ ቁጥር 1294/2015 መሠረት ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ሆኖ እንዲቋቋም ውሳኔ አሳልፏል።

በሌላ በኩል ሀገር ውስጥ የሚገኙ ስታርታፖችን ለመደገፍ መንግሥት ሕንፃ አስገንብቶ አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረገ መሆኑንም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ ተነስቷል።

# የቴክኖሎጂው አሻራ በታሪካዊቷ ከተማ



ኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት በየካቲት ወር በጎንደር ከተማ ተገኝቶ ነበር። ከቴክኖሎጂዉ ልማት ባሻገር በወጣቶች እና ታዳጊዎች ላይ መልካም ዘር መዝራት የዘርፋን ዓለማቀፍ ተወዳዳሪነት ከፍ ለማድረግ ወሳኝ ነው። ለዚሁ ተግባር ትልቅ ግብዓት ይሆን ዘንድ በጎንደር ከተማ በሚገኙ ሦስት ትምህርት ቤቶች ላይ የኤ. አይ ከበባት ምስረታ ተካሂዷል።





መሰል ክበባትን በተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች ምስረታ ሲያከናዉን የቆየዉ ኢንስቲትዩቱ አሁን ደግሞ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሞዴል አዳሪ ትምህርት ቤት፣ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ ትምህርት ቤት እና ፋሲለደስ ትምህርት ቤቶች የክበብ ምስረታዉን አከናዉኗል።

የኤ. አይ ክበባቱ ኢንስቲትዩቱ ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር የመሰረታቸዉ ናቸዉ።

ኢንስቲትዩቱ ከክበባት ምስረት ባሻገር የኤ. አይ ቴክኖሎጂን በጋራ ለማልማት ብሎም የጥናትና ምርምር ስራዎችን በጋራ ለማድረግ የሚያስችል ስምምነት ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ ጋር ተፈራርሟል።

# ኢንስቲትዩት የኤ.አዩ ዘር የመዝሪት ሂደት

AI UniPod
powered by timbuktoo



ኤ. አይ ዩኒፖድ በኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና በተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም ትብብር በቲምቡክቱ ኢንሼቲቭ አማካኝነት የተገነባ ነው።

የኢ. ፌ. ዴ. ሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ በምርቃ መርሐ ግብሩ ላይ ባስተላለፉት መልዕክት ኤ. አይ ዩኒፖድ በጠንካራ ተቋማት ትብብር የተመሰረተ የፈጠራ እና የቴክኖሎጂ ማበልጸጊያ ማዕከል መሆኑን አንስተዋል። ማዕከሉ ሀሳቦች ወደ ተግባር የሚቀየሩብት በአፍሪካውያን፤ ለአፍሪካውያን የሚያገለግል ይሆናል ብለዋል።

የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ወርቁ ጋቸና (ዶ/ ር) ኤ. አይ ዩኒፖድ በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ መስክ ለሚሰሩ አካላት ዘር የመዝሪት ሂደት ነው ብለዋል። ኤ. አይ ዩኒፖድ የቴክኖሎጂው ተመራማሪዎችን ከገበያው ጋር የማስተሳሰሪያ ዕድል መሆኑንም ገልጸዋል። ይህም ኢትዮጵያን በአፍሪካ የኤ. አይ ሥነ- ምህዳር አህጉራዊ የስበት ማዕከል ያደርጋታል ሲሉ ዋና ዳይሬክተሩ አመላክተዋል።














በኤ. አይ ዩኒፖድ የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ብሔራዊ የኤ. አይ የፖሊሲ አፈጻጸምን መከታተል እና ቴክኒካል አቅጣጫ በመስጠት፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ የአካዳሚክ ልህቀት እና የላቀ የምርምር አቅምን በማጎልበት በትብብር የሚሰሩ ይሆናል። ሌላኛው አጋር የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም (UNDP) በበኩሉ በተምቡክቱ ኢኒሼቲቭ አማካኝነት ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ የመሠረተ ልማት ድጋፍ እና በዘርፉ ያሉ ብቁ የቴክኖሎጂ ባለሙያዎችን የሚያቀርብ ይሆናል።

ማዕከሉ ሦስቱ ተቋማት ባደረጉት ትብብር መሰረቱን ኢትዮጵያ ያደረገ ተዓማኒ እና ዓለማቀፍ ግንኙነት ያለዉ መላዉ አፍሪካን መጥቀም የሚችል የኤ. አይ ሥነ ምህዳር ለመፍጠር መሠረት ይሆናል።

ኤ. አይ ዩኒፖድ የመስሪያ ቦታ እና የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማትን በጋራ አጣምሮ የያዘ ሲሆን ፤ አዲስ ሐሳብና ጥናት ላላቸው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች፣ በፍጥነት ለማደግና በዘርፋቸው ተፅዕኖ ለመፍጠር ዝግጁ ለሆኑ አዳዲስ ቴክኖሎጂ ፈጣሪዎች (Startups) እንዲሁም የዕውቀት አድማሳቸውን ማስፋት ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች የላቀ አበርክቶ ይኖረዋል።

የኢ. ፌ. ዴ. ሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ፣ የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት አመራሮች፣ የተባበሩት መንግሥታት ረዳት ዋና ፀሐፊ እና የዩኤንዲፒ የአፍሪካ ቀጠና ዳይሬክተር አሁና ኢዚያኮንዋ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ሳሙኤል ክፍሌ (ዶ/ ር) እንዲሁም ከፍተኛ የመንግሥት የስራ ኃላፊዎች በተገኙበት የምርቃት መርኃ ግብሩ ተከናዉኗል።





# ሲስኮ እና አዲሱ “ሲልከን ዋን G300”




ሲስኮ ሲስተምስ አዲስ የኤ. አይ ኔትወርክ ቺፕ ይፋ አደረገ።

ሲስኮ ሲስተምስ በትላልቅ የዳታ ሴንተሮች ውስጥ መረጃ በፍጥነት እንዲንቀሳቀስ የሚያስችል የኤ. አይ ኔትወርክ ቺፕ እና ራውተር አስተዋዉቋል። ሲልከን ዋን ጂ300 (Silicon One G300) ተብሎ የተሰየመው ይህ ቺፕ በተያዘዉ የአዉሮፓዊያን ዓመት አጋማሽ ላይ ለሽያጭ ይቀርባል ተብሎ ይጠበቃል።

ቺፑ ግዙፍ በሆኑ ዳታ ሴንተሮች ውስጥ ባሉ በመቶ ሺዎች በሚቆጠሩ ግንኙነቶች ላይ የኤ. አይ ሥርዓቶች ይበልጥ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማሳለጥ አስቻይ እንደሚሆን ሮይተርስ ዘግቧል።

ይህ የኤ. አይ ኔትወርክ ቺፕ ፈጣን እና የተሻለ የመፈጸም አቅም ያላቸዉን የኤ. አይ ቺፖች ለማምረት በሚያስችለዉ TSMCን 3-ናኖ ሜትር የተባለ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የሚመረት ነዉ። ከፍተኛ የዳታ ፍሰት በሚኖርበት ጊዜ የኢንተርኔት መዘግየቶች እንዳይኖሩ ለመከላከል የሚያስችሉ ልዩ ባህሪያትንም ያካትታል።

ሲስኮ ሲስተምስ ኢንተርኔትን እና ሰፊ የኮምፒውተር መረቦችን የሚያንቀሳቅሱ ሃርድዌርና ሶፍትዌሮችን የሚያመርት ዓለም አቀፍ የቴክኖሎጂ ኩባንያ ነው።

# አርቲፊሻል ኢንተለጀንስን በነጻ የት እንማር?

## የሀገር ዉስጥ ቋንቋዎችን መማር፣ የቪድዮ ሰብታይትል፣ ለጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ አልያም የትርጉም ስራዎችን መስራት የሚችል መተግበሪያ እናስተዋውቅዎ።

### ለርን ኤንድ ትራንስክራይብ ኢቲ.ላንግ

- በአማርኛ፣ አፋን ኦሮሞ፣ ትግርኛ፣ አፍ ሶማሊ እና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች ይሰራል።
- የሀገር ዉስጥ ቋንቋዎችን መማር፣ የትርጉም፣ ድምጽን ወደ ጽሁፍ መቀየር የሚያስችሉ እና ሌሎችም አማራጮች አሉት።
- መተግበሪያዉ በኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት በልጽጓል።

### አዲስ ኤ.አይ

- ለጥያቄዎች ምላሽ እና ማብራሪያ መስጠት እንዲሁም ሃሳቦችን መተርጎም ይችላል።
- ምላሾቹን በድምጽ እና በጽሁፍ በአማርኛ ቋንቋ ያቀርባል ።
- በአዲስ ኤ.አይ ስታርታፕ በልጽጓል።

### ሀሳብ ኤ.አይ

- በአፋን ኦሮሞ፣ ትግርኛ እና አማርኛ ቋንቋዎች አገልግሎት ይሰጣል።
- ድምጽ ወደ ጽሁፍ ለመቀየር፣ ለትርጉም ስራ፣ የቪዲዮ ሰብታይትል እና ካፕሽን ለመስራት ያገለግላል።
- ሀሳብ ኤ.አይ የተሰኘ ስታርታፕ አበልጽጎታል።

### ልሳን ኤ.አይ

- ትግርኛ፣አማርኛ እና እንግሊዝኛ ቋንቋዎችን መተርጎም ይችላል።
- አገልግሎቱን ድረ-ገፁ ዉስጥ በመግባት ማግኘት ይችላሉ።
- በልሳን ኤ.አይ ስታርታፕ ተሰርቷል።

# ኢትዮጵያ የአፍሪካ የቴክኖሎጂ አቅጣጫ አመላካች

"ኢትዮጵያ በዓለማችን ሁለተኛ የሆነውን የኤ. አይ ዩኒቨርሲቲ በመገንባት ላይ ትገኛለች።" ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ( ዶ/ ር)

ይህንን ንግግር ጠ/ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ( ዶ/ ር) በ6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 10ኛ መደበኛ ስብሰባ የመንግሥት የ6 ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ከምክር ቤት አባላት ለሚነሱ ጥያቄዎች ዝርዝር ምላሽ እና ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት የተናገሩት ንግግር ነው። የዚህ ወር ዕትማችን ኢትዮጵያ በኤ. አይ ቴክኖሎጂ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት እያደረገች የምትገኘውን ጥረት እና ዓለማቀፍ ተሞክሮ ምን እንደሚመስል ሊያስቃኛችሁ ወደደ።

## መሐመድ ቢን ዛይድ የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ዩኒቨርሲቲ (MBZUAI)




መሐመድ ቢን ዛይድ የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ዩኒቨርሲቲ ( MBZUAI ) ሙሉ በሙሉ በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ቴክኖሎጂ ላይ በልዩ ሁኔታ በማተኮር የትምህርት ጥናት እና ምርምር ላይ የሚሰራ በዓለም ብቸኛው የኤ. አይ ትምህርት ተቋም ነው።

በተባበሩት አረብ ኤምሬትስ አቡ ዳቢ የሚገኘው መሐመድ ቢን ዛይድ የኤ. አይ ዩኒቨርሲቲ የተቋቋመው የተባበሩት አረብ ኤምሬትስን በኤ. አይ ትምህርት፣ ፈጠራ እና ምርምር ዓለም አቀፍ መሪ አድርጎ ለማስቀመጥ ስትራቴጂካዊ ራዕይ ይዞ ነው።

እንደ ማሽን ለርኒንግ፣ ኮምፒውተር ቪዥን፣ የተፈጥሮ ቋንቋ ቅንብር እና ሮቦቲክስ ባሉ ዋና ዋና የኤ. አይ ዘርፎች በመጀመሪያ እና በድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች ትምህርት ይሰጣል።

እንዲሁም ተዛማጅ ኢንተርዲሲፕሊን ዘርፎችን ጨምሮ የተለያዩ የላቁ የአካዳሚክ ፕሮግራሞችን ያቀርባል። የመጀመሪያ ዲግሪ ፕሮግራሙ መሰረታዊ የኮምፒውተር እውቀትን ከንግድ ግንዛቤዎች እና ከእውነተኛው ዓለም የኤ. አይ አፕሊኬሽኖች ጋር ለማጣመር የተነደፈ ሲሆን፤ የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞቹ ደግሞ በጥልቅ ምርምር እና በተራቀቁ የቴክኒክ ክህሎቶች ላይ ያተኩራሉ።





መሐመድ ቢን ዛይድ የኤ. አይ ዩኒቨርሲቲ ሌላው የሚታወቀው ዓለም አቀፍ ስኮላርሺፕ በመስጠት እና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ነው። እነዚህ ስኮላርሺፖች ተማሪዎች ያለምንም የገንዘብ ጫና በትምህርታቸው ብሎም በምርምር ስራዎቻቸው ላይ ሙሉ በሙሉ እንዲያተኩሩ ለማስቻል የተዘጋጁ ናቸው።

በአጠቃላይ መሐመድ ቢን ዛይድ የኤ. አይ ዩኒቨርሲቲ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የኤ. አይ ምርምርን፣ ተግባራዊ ትምህርትን እና የሙያ እድሎችን በማጣመር ለኤ. አይ ቴክኖሎጂ የወደፊት አስተዋጽኦ ማድረግ ለሚፈልጉ ተማሪዎች ማራኪ መዳረሻ ሆኗል።


ኢትዮጵያም ከመሐመድ ቢን ዛይድ የኤ. አይ ዩኒቨርሲቲ በመከተል በዓለም ሁለተኛ የሆነውን የኤ. አይ ዩኒቨርሲቲ ልትከፍት መሆኑን የምስራች ዜና ጠ/ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ( ዶ/ ር) ይፋ ማድረጋቸው ይታወሳል። ግንባታው እየተካሄደ የሚገኘው ይህ ዩኒቨርሲቲ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ ወደ ስራ እንደሚገባ ይጠበቃል።

ዩኒቨርሲቲው የሰውን ልጅ እሴቶች ከማሽን አስተውሎት ጋር የሚያስተሳስር፣ አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ከዓለማቀፍ ሳይንሳዊ ምርምር ጋር የሚያቀናጅ እንዲሁም አፍሪካ በቴክኖሎጂው ዘመን የራሷን አዎንታዊ አሻራ እንድታሳርፍ የሚያስችል እንደሚሆን ይጠበቃል።

በዚህም ኢትዮጵያ ብሎም አፍሪካ የራሷን እድል በራሷ የተማሩ እና በቴክኖሎጂ የሰለጠኑ ልጆቿ አማካኝነት የምትወስንበት ወሳኝ ምዕራፍ ይሆናል። ኢትዮጵያም ለዚህ ጉዞ የአቅጣጫ አመላካችነት ሚና በመወጣት ላይ ትገኛለች።

# ኤ.አዩ እና የግብርናው አብዮት

እ. ኤ. አ. በ2050 የዓለም ሕዝብ ቁጥር 9.7 ቢሊዮን እንደሚደርስ የተባበሩት መንግሥታት የዓለም ሕዝብ ቁጥር ትንበያ (World Population Prospects) ሪፖርት ያመለክታል። የምግብ ፍላጎትም በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራል። ኤ. አይ ዘላቂ ምርታማነትን በማሳደግ ይህንን እያደገ የመጣውን ፍላጎት ለማሟላት አዳዲስ መፍትሄዎችን ያቀርባል።




የኤ. አይ ሞዴሎች ከፍተኛ መረጃ የመተንተን አቅም ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃን ለገበሬዎች ለማቅረብ ያስችላሉ። የታሪክ መረጃዎችን እንዲሁም የአፈርና የአየር ሁኔታን በመተንተን ይተነብያሉ፤ ይህም ለገበሬዎች ምርታቸውን እንዲያሳድጉ እና የአቅርቦት ሰንሰለቶችን በብቃት እንዲያስተዳድሩ ይረዳቸዋል።

በኤ. አይ የሚመራ የመስኖ ግብርና የአፈር እርጥበት መጠንን እና የአየር ሁኔታ ትንበያን በመተንተን የውሃ አጠቃቀምን ያስተካክላል። ዓለምአቀፋ የውሃ አስተዳደር ኢንስቲትዩት (IWMI) ያደረገው ጥናት እንደሚያመለክተው በኤ. አይ ላይ የተመሰረቱ የመስኖ ሥርዓቶች የሰብል ምርትን ሳይቀንሱ ወይም ሳይነኩ የውሃ አጠቃቀምን እስከ 30 በመቶ ሊቀንሱ ይችላሉ።



የኤ. አይ ቴክኖሎጂ የግሪንሀውስ ጋዝ ልቀትን የሚቀንሱ አሰራሮችን ገበሬዎች እንዲከተሉ ይረዳል።

የኤ. አይ ሥርዓቶች ከሴንሰሮች፣ ከድሮኖች እና ከሳተላይቶች የሚገኙ መረጃዎችን በመተንተን የአፈር ሁኔታን፣ የሰብል እና የአየር ትንበያን የመሰሉ ቅጽበታዊ መረጃዎችን መስጠት ይችላሉ። በዚህም የምርት ብክነትን በመቀነስ ምርታማነትን ለመጨመር ያስችላሉ።

ኮምፒውተር ቪዥን በግብርና ውስጥ ምስሎችን በመተንተን የሰብሎችን ጤና ለመከታተል፣ ተባዮችን እና በሽታዎችን ለመለየት እንዲሁም የአፈር ሁኔታን ለመገምገም ያገለግላል።

ሮቦቶች የመዝራት፣ አረም የማረም እና ምርት መሰብሰብን የመሰሉ አድካሚ ስራዎችን በብቃት በማከናወን ምርታማነትን ይጨምራሉ።

በኤ. አይ የሚሰሩ ራስ ገዝ ( ሾፌር አልባ) ትራክተሮች እና አዝመራ ሰብሳቢዎች የመዝራት፣ አረም የማረም እና ምርት የመሰብሰብ ስራዎችን በትክክል እና በብቃት ማከናወን ይችላሉ። እነዚህ ማሽኖች የጉልበት ወጪን ከመቀነሳቸውም በላይ የሥራ ቅልጥፍናን ይጨምራሉ።

በኤ. አይ የሚሰሩ ድሮኖች እና የሳተላይት ምስሎች ሰብሎችን ያለማቋረጥ በመከታተል ተባዮችን፣ በሽታዎች እና የንጥረ- ምግብ እጥረት ችግሮችን ለመለየት ያስችላሉ።

የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩትም ለግብርናው ዘርፍ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው። በግብርና ዘርፍ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ኤ. አይን እየተገለገለበት ይገኛል። ለአብነትም የቡና እና የቲማቲም በሽታን ለመለየት የሚያስችሉ ሲስተሞች አልምቶ ጥቅም ላይ አውሏል።



# EFPAPP የዲጂታል ዘመኑ ፖሊስ




የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ራሱን በቴክኖሎጂ አደራጅቶ ወንጀልን ለመከላከል እና የዜጎችን ደህንነት ለመጠበቅ ከኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ጋር በጋራ በመሆን ኢንስቲትዩቱ አበልፅጎ በሰጠው የወንጀል ጥቆማ መስጫ ሞባይል መተግበሪያ አማካኝነት የተለያዩ የወንጀል ጥቆማዎችን እየተቀበለ ይገኛል፡፡

ኢንስቲትዩቱ ከፌደራል ፖሊስ ጋር በመተባበር EFPApp የሚል መጠርያ ያለውን መተግበሪያ በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አማካኝነት ግንቦት 15 ቀን 2016 ዓ.ም ተመርቆ ስራ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ የፖሊስን ድጋፍ የሚፈልጉ የወንጀል ጥቆማዎችን በመቀበል ላይ ነው፡፡ ዜጎችም ሲስተሙን በመጠቀም ሲፈፀም ያዩትን ማንኛውንም ወንጀል ጥቆማ በማድረስ ላይ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ያለማው ይህ ሲስተም ዜጎች ሲፈፀም ያዩትን ማንኛውንም ወንጀል በሞባይል ስልኮቻቸው አማካኝነት ካሉበት ሆነው ለፖሊስ ጥቆማ ለመስጠትና የደረሰበትን ሁኔታ ለመከታተል የሚያስችል የቴክኖሎጂ ስርዓት ነው፡፡

መተግበሪያው ዜጎች በየትኛውም ቦታና ሁኔታ ሲፈፀም ያዩትን ወንጀል በፎቶ፣ በቪድዮ፣ በድምፅ፣ በጽሑፍ እና በሌሎች መንገዶች ለፖሊስ ጥቆማ እንዲልኩ አስችሏቸዋል፡፡




የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ከህብረተሰቡ የሚደርሱ የወንጀል ጥቆማዎችን ለመቀበል የሚያስችለውን የEFPApp ስርዓት ከማልማቱ ጎን ለጎን ከሲስተሙ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የሰው ኃይልን ለማብቃት የሚያስችል የእውቀት እና የክህሎት ስልጠና ሰጥቷል።

ዜጎች መተግበሪያውን ሲጠቀሙ የጥቆማ መረጃዎችን ለፖሊስ ካደረሱ በኋላ ጉዳዩ የደረሰበትን ደረጃ መከታተል ማስቻሉ ሌላው የመተግበሪያው ገፅታ ነው። ጠቋሚዎች ማንነታቸው ሳይታወቅ መረጃ መስጠት ከፈለጉም መተግበሪያ አማራጩን አካቷል። ሲስተሙ የፖሊስ ዋና ተግባር የሆነውን ወንጀልን የመከላከልና የመቆጣጠር ሂደት ከማሳለጡ በተጨማሪ ለምርመራ መነሻ የሚሆኑ ሀሳቦችን ለማግኘት፣ ወንጀለኞችን ለሕግ ለማቅረብ እና ፍትሕን ለማስፈን  እያስቻለ ነው።




መተግበሪያው በዱባይ በተካሄደው ዓመታዊ የዓለም ፖሊስ ጉባኤ (World Police Summit) ላይ በዓለማቀፍ ደረጃ ምርጥ የፖሊስ መተግበሪያ (Best Police Application) በሚል ዘርፍ አንደኛ ደረጃን ይዟል። EFPApp መተግበሪ በኤ. አይ ቴክኖሎጂ የታገዘ፣ ለአጠቃቀም ምቹ እና ለማህበረሰባዊ ደህንነትም ጉልህ ሚናን በመጫወቱ በዓለማቀፍ ደረጃ ውድድሩን እንዲያሸንፍ አስችሎታል።

የሞባይል መተግበሪያው ከአዲስ አበባ በተጨማሪ በድሬድዋ ከተማ አስተዳደርም ከህብረተሰቡ ለሚደርሱ ጥቆማዎች ምላሽ በመስጠት ላይ ይገኛል ። አሁን ላይም ሲስተሙን ወደ ተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች በማስፋፋት ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስራ እየተሰራ ይገኛል።

መተግበሪያው ወደ ስራ ከገባባት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ከአስር ሺህ በላይ የወንጀል ጥቆማዎች የተላኩበት ሲሆን፤ ከመቶ ሺህ በላይ ሰዎች ከፕሌይ ስቶር እና አፕ ስቶር አውርደው እንደጫኑት መረጃዎች ያሳያሉ።

# የአይን ህመምን በሞባይል ስልክ የሚለየው . . .

የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት በዓለማቀፍ ደረጃ ተነባቢነትን ያገኙ እና በማህበረሰባዊ ፋይዳቸው የላቁ የጥናት እና ምርምር ውጤቶቹን በዓለማቀፍ ጆርናሎች ላይ እንዲታተሙ እያደረገ ይገኛል።

እስካሁን ስልሳ የሚደርሱ የጥናት ውጤቶች ለሕትመት በቅተዋል። በዛሬው የዲጂታል መጽሔት ዕትማችን ከኢንስቲትዩቱ የጥናት ስራዎች አንዱን ልናስቃኛችሁ ወደናል።

ጥናቱ በዕውቀት ሽግግር ላይ የተመሰረተ ቀላልና ፈጣን የሞባይል ኔት ሞዴል ለስኳር በሽታ የዓይን ህመም (Diabetic Retinopathy) ምርመራ ይሰኛል። ጥናቱ በዘርፉ ሰፊ እውቀት ባላቸው ኢትዮጵያውያን ተመራማሪዎች በጋራ የተሰራ ነው።

በዓለማችን ላይ ለዓይነ ስውርነት ከሚዳርጉ ምክንያቶች መካከል በስኳር በሽታ ምክንያት የሚመጣ የዓይን ህመም ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል። በኢትዮጵያ ደግሞ ችግሩ የከፋ ነው። ለአንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ህዝብ የሚገኘው የአይን ስፔሻሊስት ሐኪም አንድ ብቻ ነው። ይህ ጥናት ይህንን ሰፊ ክፍተት የሰው ሰራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ እንዴት መሙላት እንደሚችል አዲስ ብርሃን የፈነጠቀ ነው።




ጥናቱ እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ የስኳር ህመምተኞች መካከል 19 በመቶ የሚሆኑት ለዚህ የአይን ህመም የተጋለጡ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ 10 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ለዓይነ ስውርነት የሚያሰጋ ደረጃ ላይ ይገኛሉ።

ብዙውን ጊዜ የሰው ሰራሽ አስተውሎት ሞዴሎች ከፍተኛ የኮምፒውተር አቅም ስለሚጠይቁ በተራ ስልኮች ላይ ለመጠቀም አስቸጋሪ ናቸው። ተመራማሪዎቹ ግን 'Knowledge Distillation' የተባለ ዘዴን በመጠቀም፤ የአንድን ትልቅና ውስብስብ ሞዴል እውቀት ወደ ትንሽና ቀልጣፋ ሞዴል (MobileNet) አዛውረዋል። ይህም ምርመራን በቀላል በሆነ መንገድ በሞባይል ስልኮችና ራቅ ባሉ የጤና ተቋማት ውስጥ ለማከናወን ያስችላል።

ይህ አዲስ የኤ. አይ ሞዴል የታካሚዎችን የዓይን ምስል አይቶ በሽታው መኖር አለመኖሩን በመለየት 98.38 በመቶ ትክክለኛነት አስመዝግቧል። በሽታው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለመለየት ደግሞ 93.03 በመቶ ስኬታማ ሆኗል።

የጥናቱ ፋይዳ፦

* ታካሚዎች ቅድመ ምርመራ እንዲያደርጉ በማስቻል ዓይነስውርነት መከላከል ያስችላል፣
* የሐኪሞችን የምርመራ ጊዜ ከመቆጠቡም በላይ በቂ ስፔሻሊስት በሌለባቸው አካባቢዎች እንደ ረዳት ሆኖ ያገለግላል፣
* ውድ የሆኑ የምርመራ መሳሪያዎችን ሳይጠብቁ በቴክኖሎጂ የታገዘ የጤና አገልግሎትን ለሁሉም ተደራሽ ለማድረግ ይረዳል።

ይህ ጥናት በዓለም አቀፍ ደረጃ እጅግ ታዋቂና ተሰሚነት ባለው Nature Portfolio ስር በሚገኘው Scientific Reports በተሰኘው የሳይንሳዊ መጽሔት (Journal) እ. ኤ. አ. የካቲት 2025 ላይ ታትሟል።

የዚህ ጥናት ውጤትን ለማንበብ ይንን ሊንክ ይጠቀሙ።
https://www.nature.com/articles/s41598-025-30893-7



# የኢንስቲትዩቱ ዲጂታል ቤተ-መጽሐፍት




የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት በአዲሱ የዋና መሥሪያ ቤት ሕንጻ ካካተታቸው የተለያዩ አገልግሎት መስጫዎች መካከል አንዱ ዲጂታል ቤተ- መጽሐፍት ነው።

ቤተ- መጽሐፍቱ ለኢንስቲትዩቱ ማሕበረሰብ የኤ. አይ ምርምር እና ልማት ስራዎችን ለማከናወን አጋዥ የሆኑ የዘርፉን ታዋቂ መጽሐፍቶቸ፣ ጆርናሎች፣ የምርምር ጽሁፎች እና የፖሊሲ ማዕቀፎችን የበይነ መረብ የንባብ ዕድሎችን ጨምሮ በአካል መጽሐፍቱን ማግኘት በሚቻልበት አማራጭ ተደራጅቶ ወደ ስራ ገብቷል።

ይህም የዘርፉ ተመራማሪዎች፣ በኢንስቲትዩቱ ስታርታፕ ማዕከል እና ዩኒፖድ የታቀፉ ስራ ፈጣሪዎች እንዲሁም ተማሪዎች እንደ ዓለማቀፍ አቻዎቻቸው ዘርፉን የተመለከቱ የንባብ ግብዓቶችን ከኢንስቲትዩቱ ርቀው ሳይሄዱ እንዲያገኙ ያስችላል።

## የቤተ- መጽሐፍቱ ተልዕኮ

ቤተ መጻሕፍቱ በኢንስቲትዩቱ ባለሞያዎች በለሙ እና የኤ. አይ ቴክኖሎጂን ከቤተ- መጻሕፍት ሥነ- ዘዴ ጋር ባጣመሩ የዲጂታል አማራጮች የተደራጀ ነው። በመሆኑም በጠንካራ መሠረት ላይ የተዋቀረ እና በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ዘርፍ ዙሪያ የእውቀት መሻት ባሕልን በኢንስቲትዩቱ ውስጥ ለመገንባት የተዘጋጀ የእውቀት ምንጭ በመሆን ያገለግላል። የቤተ- መጻሕፍቱ የተደራጀ የመረጃ ቋት የሚከተሉተን አራት ቁልፍ የኤ. አይ ማህበረሰብ ፍላጎትን ያማከለ ነው።

እነዚህም፡-

* የኢንስቲትዩቱ ተመራማሪዎች እና ሰራተኞች፡- በዘርፉ ራስን በየዕለቱ ማብቃት እና ብሔራዊ ተነሳሽነትን ማጎልበት።
* ጀማሪ ስራ ፈጣሪዎች፡- በኢንስቲትዩቱ የኤ. አይ ስታርታፕ እና በኤ. አይ ዩኒፖድ ማዕከላት ፈጠራን ማነሳሳት።
* ቀጣዩ ትውልድ፡- የኤ. አይ ሰመር ካምፕ ተሳታፊ ታዳጊዎችን ማብቃት።
* የአካዳሚክ ልህቀት፡- በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ዙሪያ እየተማሩ የሚገኙ የማስተርስ እና የዶክትሬት እጩዎችን መደገፍ ናቸው።

## የቤተ- መጻሕፍቱ ገፅታ

ዲጂታል ቤተ መጻሕፍቱ የእውቀት ፍሰትን የበለጠ አስደሳች የሚያደርጉ የተለያዩ ገጽታዎችን ያካተተ ነው።

* የእያንዳንዱን ተጠቃሚ ፍላጎት ያገናዘበ የኤ. አይ ሥርዓት፡- ልክ እንደ ኔትፍሊክስ እና ዩቲዩብ ደጂታል ቤተ- መጻሕፍቱም የማሽን ለርኒንግ ስልተቀመሮችን በመጠቀም የተጠቃሚዎችን የንባብ ታሪክ የመገንዘብ እና ተመሳሳይ ቀጣይ ፍላጎቶችን የመጠቆም አማራጮችን አካቷል።
* ስማርት ቡክማርኪንግ፡- የቤተ- መጻሕፍቱ ዲጂታል ሥርዓት የተጠቃሚዎችን የንባብ ሂደት በመመዝገብ፤ ተጠቃሚዎች በማንኛውም ጊዜ ንባብ ካቆሙበት ቦታ እንዲቀጥሉ ያስችላቸዋል።
* ቅልቅል ተለማጭነት፡- ለጥልቅ ትኩረት እና ተጠቃሚዎች በስክሪን ላይ የሚያሳልፉትን ጊዜ ለመቀነስ በማሰብ መደበኛ መጻሕፍት እና ብሔራዊ የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ፖሊሲ ዕትም ስብስቦችን የያዘ ነው።










* የምርምር ውጤቶችን በቀላሉ ለማግኘት፡- ተጠቃሚዎች እንደ IEEE እና Springer ባሉ ታዋቂ ጆርናሎች ላይ ለሕትመት የበቁ የኢንስቲትዩቱን የጥናት እና ምርምር ስራዎች በቀጥታ እንዲያገኙ ያስችላል። ይህም የዓለማቀፍ የኤ. አይ አዝማሚያዎችን ከአካባቢያዊ ዐውድ ጋር አጣምሮ ለመረዳት ዕድል ይሰጣል።

## ከስብስቦቻችን መካከል

ዲጂታል ቤተ መጻሕፍቱ ከ200 በላይ በክፍያ የደንበኝነት ምዝገባ የሚገኙ መጻሕፍትን ይዟል። እንደ O’ Reilly እና Springer የመሳሰሉ በጣም ተፈላጊ ስብስቦችንም አካቷል። የመጽሐፍት ስብስቦቹ በዘርፉ በዓለማቀፍ ደረጃ የቀዳሚነት ሥፍራን የያዙ በመሆናቸው ለተጠቃሚዎች ከፍተኛ የእውቀት ደረጃን በማቅረብ ብቁ የሰው ኃይል ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት ያግዛሉ።

በቤተ- መጻሕፍቱ ከሚገኙ መጽሐፍት መካከል፡-

* Artificial Intelligence: A Modern Approach by Stuart Russell and Peter Norvig : The world’s most cited AI textbook.
* Hands-On Machine Learning with Scikit-Learn, Keras, and TensorFlow by Aurélien Géron : The definitive guide for building production-ready systems.
* Deep Learning by Ian Goodfellow, Yoshua Bengio, and Aaron Courville : The mathematical foundation for modern neural network research.
* Generative Deep Learning by David Foster: A comprehensive deep dive into GANs and Diffusion models.
* Pattern Recognition and Machine Learning by Christopher Bishop: A fundamental text for statistical AI development.



# ኤ.አዩ እና ፖሊሲ




የዓለማቀፍ የኤ. አይ የሥነ- ምግባር ፖሊሲ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ደህንነቱ በተጠበቀ፣ ፍትሐዊ እና ከሰው ደህንነት ጋር በተጣጣመ መልኩ እንዲዳብር ለማድረግ ሁለንተናዊ የአስተዳደር ማዕቀፍ ለመመስረት ያለመ ነው። የኤ. አይ ስርዓቶች ድንበር ተሻግረው ስለሚሰሩ እንዲህ ያለው ፖሊሲ የተበታተኑ የቁጥጥር አቀራረቦችን ለማስታረቅ ጉልህ ሚና እንዳለው ይታመናል። ለአብነትም በአውሮፓ ህብረት የወጣው እንደ “Europe’s stringent risk classifications” ፣በአሜሪካ “America’s light-touch industry guidance” እና  በኢስያ “Asia’s state-led innovation models” የመሳሰሉትን የሰውሰራሽ አስተውሎት የሥነምግባር ፖሊሲ ወደ አንድ የተቀናጀ ዓለማቀፍ ደረጃ ለማምጣት ያቀደ ነው።

ይህንን ገዢ ሃሳብ መሰረት በማድረግ በዓለማችን የሚገኙ ግዙፍ የሶፍትዌርና የኤ. አይ ምርት አቅራቢ ኩባንያዎች የሰውሰራሽ አስተውሎት የሥነ ምግባር ፖሊሲዎቻቸውን ይቀርጻሉ። ለማሳያ ያክል የ“Systems, Applications & Products in Data Processing” ኩባንያ በምጻሩ “ SAP” ተብሎ የሚጠራውን በጥቂቱ እናስተዋውቃችሁ።

“SAP Global AI Ethics Policy” በድረ- ገጹ በ2024 ይፋ ባደረገው የፖሊሲ ቅጂው ላይ በዩኔስኮ ስለ ሥነ ምግባራዊ ኤ. አይ የተሰጠ ግብረመልስን መሰረት ያደረገ የፖሊሲ ማዕቀፍ መሆኑን ጠቅሷል።

በዚህ የፖሊሲ ማዕቀፋ ውስጥ በርካታ በፍጹም የማይጣሱ ዋና ዋና መርሆች አሉ።

* ግልጸኝነት፦ የኤ. አይ ሥርዓቶች የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ሊተረጎሙ እና ለምርመራ ክፍት እንዲሆኑ ይጠይቃል።
* ፍትሃዊነት እና አድልዎ አለመፈጸም፦ ማህበራዊ ኢ- ፍትሀዊነትን ሊያባብሱ የሚችሉ የአልጎሪዝም አድሎአዊ ድርጊቶች በንቃት እንዲወገዱ ያዛል።
* ተጠያቂነት፦ በራስ ገዝ ስርዓቶች ለሚደርሱ ጉዳቶች ከአበልጻጊዎች ሲስተሙን ስራ ላይ እስካዋሉት አካላት ድረስ ግልጽ የሆነ የሕግ ተጠያቂነትን ያስቀምጣል።
* ግላዊነት እና የዳታ አስተዳደር፦ የተጠቃሚዎችን ስምምነት እና ዳታቸው ያላግባብ እንዳይሰበሰብ ወይም የመሰብሰብ ሂደትን መቀነስ ላይ አፅንዖት ይሰጣል።
* የሰው ልጅ ራስ ገዝነት፦ ኤ. አይ የሰውን ዳኝነት የሚፈልጉ በተለይም እንደ ፍትሕ ወይም የጤና አጠባበቅ ባሉ ከፍተኛ ጉዳዮች ውስጥ ማገዝ እንጂ የሰውን ልጅ መተካት እንደሌለበት ያረጋግጣል።

እነዚህን እሴቶች ተግባራዊ ለማድረግ ፖሊሲው ጠንካራ የቅድመ- ሥምሪት ወይም ሲስተሙ አገልግሎት ላይ ከመዋሉ በፊት የሚደረጉ ኦዲቶችን፣ የሶስተኛ ወገን ቁጥጥር ኮሚቴዎችን እና የበለጸገው ሲስተም ችግር ከማስከተሉ በፊት በሲስተሙ ውስጥ የሰው ልጆችን ጣልቃ የመግባት የአሰራር ሂደቶችን ያቀርባል። ይሁንና የትግበራው ሂደት በርካታ ፍጭቶች ሊያጋጥሙት ይችላል። ለምሳሌ "ግላዊነትን" ወይም "ነፃ ንግግር"ን ትርጉም ለመስጠት የባህል ልዩነቶች ተግዳሮት ሊኖሩ ይችላሉ። በሌላ በኩል ኩባንያዎች ፖሊሲው ፈጠራን ያቀጭጫል በሚል ይህንን የሥነ ምግባር ፖሊሲ መርሖችን ይቃወማሉ።

እነዚህ መሰናክሎች ቢኖሩም ፖሊሲው በዓለማቀፍ ደረጃ የተጣጣመ የሥነ ምግባር መነሻ በመሆን በፉክክር ጫና ምክንያት የሚከሰትን የሥነ ምግባር ጥሰትን እና ከደረጃ በታች የሆኑ የኤ. አይ ምርቶችን በመከላከል፤ ኤ. አይ ከስርዓታዊ ስጋት ምንጭነት ይልቅ ለጋራ ብልጽግና መሣሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ጥብቅና ይቆማል።

# እንግዳችን . . .



> " ኢትዮጵያ የራሷን ታሪክ በራሷ ቴክኖሎጂ የምትተርክ ሀገር እንድትሆን የዲጂታል አምባሳደርነት ሚናዬን እወጣለሁ"
>
> ብርሃን ታፈሠ

ብርሃን ታፈሠ ይባላል። በሜካኒካል ምህንድስና የመጀመሪያ ዲግሪውን ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ አግኝቷል። የማስተርስ ዲግሪውን ደግሞ በህንድ ሀገር ከሚገኘው ሻርዳ ዩኒቨርሲቲ ተቀብሏል። በተለያዩ የመንግሥትና የግል ተቋማት በምርት ዲዛይንና ልማት የሥራ ልምድ አለው። በተጨማሪም ከማይክሮሶፍት፣ ሊንክዲን ለርኒንግ እና አሊሰን ከመሰሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት በጄኔሬቲቭ ኤ. አይ እና ፕሮምፕት ኢንጂነሪንግ ስልጠናዎችን ወስዷል። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የሮቦቲክስ ዲዛይን መሐንዲስ ሆኖ እየሰራ ይገኛል። ከእርሱ ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል። መልካም ንባብ!

**ጥያቄ፦ የትምህርት ዝግጅትህንና የሥራ ተሞክሮህን ባጭሩ ብታጋራን?**

**ብርሃን፦** በመጀመሪያ ለዚህ ግብዣ አመሰግናለሁ። እኔ የኢኖቬቲቭ ምርት ዲዛይን መሐንዲስና የጄኔሬቲቭ ኤ. አይ ባለሙያ ነኝ። ትምህርቴን በተመለከተ የመጀመሪያ ዲግሪዬን ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፣ ሁለተኛ ዲግሪዬን ደግሞ ከህንድ ሻርዳ ዩኒቨርሲቲ በሜካኒካል ምህንድስና ተመርቄያለሁ።

ከመደበኛ ትምህርቴ በተጨማሪ በጄኔሬቲቭ ኤ. አይ እና ፕሮምፕት ኢንጂነሪንግ ላይ ከማይክሮሶፍት እና ሊንክዲን ለርኒንግ መሰል ተቋማት ሙያዊ እውቅና አግኝቻለሁ። በሥራ ተሞክሮዬም በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ አቪዬሽን ዩኒቨርሲቲ እና በሸፋን ሶሉሽንስ ሰርቻለሁ። በአሁኑ ወቅት ደግሞ በኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ውስጥ እያገለገልኩ እገኛለሁ።

**ጥያቄ፦ በኢንስቲትዩቱ ውስጥ ያንተ የሥራ ድርሻ ምንድነው?**

**ብርሃን፦** የሮቦቲክስ ዲዛይን መሐንዲስ ነኝ። ሮቦቶችን ከሐሳብ ንድፍ ጀምሮ በሲሙሌሽን እና በ3 ዲ ሞዴሊንግ (3D Modeling) ለዓይን ሳቢ፣ ለተጠቃሚ ምቹ እና ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ በዲዛይን መሪነት እየሰራሁ እገኛለሁ። ካለፈው አንድ ዓመት ወዲህ ደግሞ በጄኔሬቲቭ ኤ. አይ መስክ ላይ በስፋት እየሰራሁ እገኛለሁ።

**ጥያቄ፦ በኢንስቲትዩቱ ቆይታህ ያንተ ድርሻ ምንድነው?**

**ብርሃን፦** የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት መመስረት ሀገራችንን የቴክኖሎጂ ተቀባይ ብቻ ሳትሆን የፈጠራ ምንጭና የአፍሪካ የኤ. አይ ማዕከል መሆን እንደምትችል ያሳየ ትልቅ ክስተት ነው። እኔም በዚህ ታሪካዊ ጉዞ ውስጥ እንደ አንድ ባለሙያ በርካታ ተግባራት አከናውኛለሁ።

በኢንስቲትዩቱ የሚሰሩ ሮቦቶች ከቴክኒካዊ ብቃታቸው ባለፈ፣ ማራኪና ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የዲዛይን እሴት እንዲኖራቸው አድርጌያለሁ። ከሐሳብ ንድፍ እስከ 3 ዲ ሞዴሊንግ ያለውን ሂደት በመምራት፤ ሮቦቶቹ ለተጠቃሚ ምቹና ለዓይን ሳቢ እንዲሆኑ ከቡድን አጋሮቼ ጋር ሰርቻለሁ። ቴክኖሎጂው በሀገራችን አዲስ በነበረበት ወቅት ለክሬቲቭ ሥራዎች እንዴት እንደሚውል በተግባር በማሳየት የራሴን ሚና ተጫውቻለሁ።

**ጥያቄ፦ በጄኔሬቲቭ ኤ. አይ ዙሪያ የምታደርገው እንቅስቃሴ በብዙዎች ዘንድ ይታወቃል። በዚህ ላይ ያለህን ልምድ ብታብራራልን?**



**ብርሃን፦** አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ያልገባበት የሙያ መስክ የለም። እኔም የምህንድስና ልምዴን ከኤ. አይ ጋር በማቀናጀት አዳዲስ ነገሮችን እየሰራሁ ነው። ቀደም ሲል ምርቶችን በኮምፒውተር ዲዛይን ማድረግና በሲሙሌሽን መፈተን የዕለት ተዕለት ሥራዬ ነበር። ኤ. አይ ግን ይህንን የፈጠራ አድማስ ይበልጥ አስፍቶልኛል።

ባለፈው አንድ ዓመት የምህንድስና እውቀቴን ከኤ. አይ ጋር በማጣመር ማራኪ የማስታወቂያ ይዘቶችን፣ ፊልሞችን እና ዲጂታል ጥበቦችን ስሰራ ቆይቻለሁ። “ጄኔሬቲቭ ኤ. አይ ለክሬቲቭስ” በሚል ርዕስ በአማርኛ ቋንቋ የ10 ክፍሎች ስልጠና አዘጋጅቼ ለብዙዎች አቅርቤያለሁ። ይህም ቴክኖሎጂውን በሥነ-ምግባርና በኃላፊነት እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ግንዛቤ ለመፍጠር የረዳ ነበር።

**ጥያቄ፦ በሶሻል ሚዲያ ፕላትፎርሞች ላይ ንቁ ተሳትፎ ታደርጋለህ። ምን ዓይነት ይዘቶችን ነው የምታጋራው?**

**ብርሃን፦** አብዛኛው ይዘቶቼ በቴክኖሎጂ፣ በምርት ዲዛይን እና በኤ. አይ ላይ ያተኮሩ ናቸው። ለምሳሌ የኢትዮጵያ አየር መንገድ Airbus A350-1000 አውሮፕላን በማስገባቱ የተሰማኝን ኩራት ለመግለጽ የሰራሁት የ3 ዲ ሞዴል (Visualization) በዓለም አቀፍ ደረጃ ትኩረት ስቧል። እንደ Dassault Systèmes እና DMD USA ያሉ ትላልቅ

ኩባንያዎች ሥራዬን በገጻቸው አጋርተውታል። ሌላው በኤ. አይ አማካኝነት የፈጠርኳት “ቆንጂት” የተሰኘችው የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት ዲጂታል አርቲስት ናት። በእነዚህ መድረኮች የማጋራቸው ይዘቶች ዓላማቸው ማስተማር፣ ማነሳሳት እና የወደፊቱን ቴክኖሎጂ ዛሬ ላይ ሆኖ ማሳየት ነው።

**ጥያቄ፦ ኤ. አይ የሰውን ልጅ ሥራ ይነጥቃል የሚል ስጋት በአንዳንዶች ዘንድ ይነሳል። ያንተ ምልከታ ምንድነው?**

ብርሃን፦ ኤ. አይ ሥራን አይነጥቅም፤ ነገር ግን አሠራራችንን ይቀይረዋል። አዳዲስ የሥራ ዕድሎችንም ይፈጥራል። ለአብነትም፦ ፕሮምፕት ኢንጂነሮች፣ የኤ. አይ ሥነ- ምግባር ባለሙያዎች እና የአውቶሜሽን አስተዳዳሪዎች ወዘተ. ተጠቃሽ ናቸው።

ዋናው ጥያቄ “ኤ. አይ ሥራ ይነጥቀናል ወይ?” ሳይሆን “ከቴክኖሎጂው ጋር እኩል እየተራመድን ነው ወይ?” የሚለው መሆን አለበት። ኤ. አይን የሚጠቀም ዶክተር፣ ጠበቃ ወይም መሐንዲስ ኤ. አይን ከማይጠቀሙት በበለጠ ፈጣንና ውጤታማ ይሆናል። ራሳቸውን የማያሻሽሉ ባለሙያዎች ግን ወደኋላ የመቅረት አደጋ ይገጥማቸዋል ብዩ አምናለሁ።

**ጥያቄ፦ በቀጣይ ምን ለማሳካት አቅደሃል?**

ብርሃን፦ ሁለት ዋና ዋና ግቦች አሉኝ፦ አንደኛው “አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ለሁሉም!” በሚለው የኢንስቲትዩታችን መሪ ቃል ቴክኖሎጂው ለሀገር በቀል ችግሮች መፍትሄ እንዲሆን መስራት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የኢትዮጵያን ታሪክ፣ ባህልና እሴት በዘመናዊ የኤ. አይ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ለዓለም ማስተዋወቅ ነው። ኢትዮጵያ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ብቻ ሳትሆን የራሷን ታሪክ በራሷ ቴክኖሎጂ የምትተርክ ሀገር እንድትሆን የበኩሌን እወጣለሁ።

**ጥያቄ፦ በመጨረሻ የምታስተላልፈው መልዕክት ካለ?**

ብርሃን፦ ዛሬ በእጃችን ያለው ስማርት ስልክ ትልቅ የአስተውሎት (Intelligence) አቅም አለው። ይህንን አቅም ለጨዋታ ብቻ ሳይሆን ለአዳዲስ ክህሎት መማሪያ እንጠቀምበት። ኤ. አይን ስንጠቀም ደግሞ በኃላፊነት ይሁን እላለሁ፤ በኤ. አይ የተሰራ ሥራን “በኤ. አይ የተሰራ ነው” ብሎ ማሳወቅ ተገቢ ነው። የሰውን ስም የሚያጠፉ ወይም ማኅበረሰብን የሚያውኩ ይዘቶችን ከመፍጠር እንቆጠብ።

# ከኤ . አዩ ስታርታፕ ማዕከል እስከ ዓለማቀፋዊ ተፅዕኖ




አርቲፊሻል ኢንተለጀንስን በመጠቀም የኢትዮጵያን ትምህርት ለማዘመንና ተደራሽ ለማድረግ የበኩሉን እየተወጣ ያለ ስታርታፕ- ግሎብ ዶክ አካዳሚ

በኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ኤ. አይ ስታርታፕ ማዕከል ተወዳድረዉ ከገቡ 200 ስታርታፖች መካከል አንዱ ግሎብ ዶክ አካዳሚ (GlobeDock Academy) ሲሆን አቶ ኪሩቤል አክሊሉ የዚህ ስታርታፕ መስራች እና ዋና ስራ አስፈጻሚ ናቸዉ።

ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ባደረጉት ቆይታ ስታርታፖቻቸው በኢትዮጵያ የትምህርት ተደራሽነት እና ጥራት መካከል ያለውን ሰፊ ክፍተት ለመሙላት በቁርጠኝነት እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል። ግሎብ ዶክ አካዳሚ የሀገሪቱን ብሔራዊ ሥርዓተ- ትምህርት ወደ ዲጂታል ቪዲዮዎች በመቀየር፣ ጥራት ያለው ትምህርት በየትኛውም የሀገሪቱ ጥግ በተለይም በገጠርና በግጭት ቀጠናዎች ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ እያደረገ ይገኛል።



አቶ ኪሩቤል እንደገለጹት የተቋማቸዉ ዋነኛ መለያው ከኤ. አይ ጋር ያለው ጥልቅ ቁርኝት ነው። የተማሪዎችን የመማር ፍጥነትና አቅም የሚያሳድጉ የኤ. አይ ቴክኖሎጂዎችን በስራ ላይ አውለዋል።

ዋና ስራ አስፈጻሚዉ ለመጽሔት ዝግጅት ክፍላችን እንደተናገሩት የኤ. አይ ስታርታፕ ማዕከል ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር የትዉዉቅ እና የትስስር መድረክ ሆኖላቸዋል። በዚህ ማዕከል ከኢንስቲትዩቱ የኤ. አይ ባለሙያዎች ጋር በቅርበት ሆነዉ ምርምር እና ሙከራ የሚያደርጉበት የስራ ቦታ፣ የጂ. ፒ. ዩ እና ሌሎችም አስፈላጊ ግብዓቶች ድጋፍ እያገኙ ነዉ።

ግሎብ ዶክ አካዳሚ በኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ኤ. አይ ስታርታፕ ማዕከል በሚደረግለት ድጋፍ በዲጂታል ፈጠራ የታገዘ ትምህርትን ለሁሉም ዜጋ ተደራሽ ለማድረግ እና ዓለማቀፋዊ ተፅዕኖ ለመፍጠር በትጋት እየሰራ ይገኛል። በቀጣይም በኢትዮጵያ የመጀመሪያው “ ኦንላይን “ ዩኒቨርሲቲ የመሆን ራዕይ ሰንቋል።

# የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ መጽሐፍት ጥቆማ

በዚህ የዲጂታል መጽሔታችን ዕትም ለንባብ የምንጠቁማችሁ መጽሐፍ በቴክኖሎጂው ዓለም አዲስ አብዮት እየፈጠረ ስለሚገኘው "Model Context Protocol (MCP)" ስለሚባለው መጽሐፍ ነው።




* ርዕስ፦ Model Context Protocol: Advanced AI Agents for Beginners
* ደራሲያን፦ መሁል ጉፕታ እና ኒላድሪ ሴን (Mehul Gupta & Niladri Sen)
* የታተመበት ዓመት፦ እ. ኤ. አ. 2025
* መጽሐፉ በ27 ምዕራፎች የተከፋፈለ እና 202 ገጾች ያሉት ነው።

## ምን ላይ ያተኩራል?

ይህ መጽሐፍ የሰው ልጅ ከኤ. አይ ጋር ያለውን ግንኙነት ከቀላል የንግግር ቻትቦቶች ባለፈ ራሳቸውን ችለው ወደሚንቀሳቀሱ የኤ. አይ ወኪሎች (Autonomous AI Agents) እንዴት ማሸጋገር እንደሚቻል የሚያሳይ ነው።

የመፅሐፉ ቁልፍ ይዘቶች፦

* ጥልቅ የኮምፒውተር ሳይንስ እውቀት ሳይጠይቅ ከ20 በላይ የMCP ሰርቨሮችን ደረጃ በደረጃ እንዴት ማዋቀር እንደሚቻል ያሳያል።
* ኤ. አይን እንደ LangChain እና Ollama ካሉ ፕላትፎርሞች ጋር በማገናኘት ውጤታማ ስራ መስራት እንደሚቻል ይተነትናል።
* የኤጀንቲክ ኤ. አይ ቴክኖሎጂን የወደፊት አቅጣጫ እና ሊከተሉ የሚችሉ ስጋቶችን ይዳስሳል።

መጽሐፉ የቴክኖሎጂ ፍላጎት ላለው ለማንኛውም ሰው የተዘጋጀ ነው። በተለይ አልሚዎች እና ዲዛይነሮች የስራ ፍሰታቸውን ለማቀላጠፍ፣ የዳታ ተንታኞችና ማርኬተሮች መረጃዎችን አውቶሜት ለማድረግ፣ ተማሪዎችና ተመራማሪዎች አዳዲስ የኤ. አይ ክህሎቶችን ለመቅሰም እንዲሁም የንግድ ባለሙያዎች የዕለት ተዕለት የቢሮ ስራዎችን በኤ. አይ በመታገዝ ለማዘመን ለሚፈልጉ በእጅጉ ይጠቅማል።

# አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ እንወቅ . . .

**ሀሉሲኔሽን (Hallucination)** በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ በተለይም በቋንቋ ሞዴሎች ውስጥ የሚከሰት ስህተት ነው። ይህም አንድ የኤ. አይ ሲስተም እውነት ያልሆነ፣ በታሪክ ያልተከሰተ ወይም ከጥሬ መረጃው ጋር የማይገናኝ ነገርን እንደ እውነተኛ መረጃ አድርጎ ሲናገር የሚታይበት ሁኔታ ነው። ሀሉሲኔሽን በመረጃ እጥረት፣ በመረጃ ስህተት ወይም ከመጠን በላይ በመገመት (Over-optimization) ሊፈጠር ይችላል።



## ፋይን ቲዩኒንግ (Fine-tuning):-

ፋይን ቲዩኒንግ (Fine-tuning) ማለት አንድን ቀድሞ የሰለጠነ (Pre-trained) ግዙፍ የኤ. አይ ሞዴል ለተወሰነ ልዩ ተግባር ወይም ዘርፍ ይበልጥ እንዲስማማ ተደርጎ በትንሽ መረጃ ዳግም የማሰልጠን ሂደት ነው። እንደ ቻት ጂፒቲ ያሉ ግዙፍ ሞዴሎች መጀመሪያ የሚሰለጥኑት በኢንተርኔት ላይ ያሉ ሁሉንም ዓይነት መረጃዎች በማንበብ ነው። ይህ “አጠቃላይ እውቀት” ይሰጣቸዋል። ነገር ግን ለአንድ ልዩ ስራ (ለምሳሌ ለህክምና ምርመራ) እንዲውሉ ሲፈለግ ከዘርፉ ጋር የተያያዙ ልዩ መረጃዎችን በመስጠት ሞዴሉ በዚያ መስክ ላይ “ባለሙያ” እንዲሆን ይደረጋል።

## ኢንፈረንስ (Inference) :-

ኢንፈረንስ (Inference) ማለት አንድ የሰለጠነ የኤ. አይ ሞዴል ከዚህ በፊት አይቶት የማያውቀውን አዲስ መረጃ ተመልክቶ ውሳኔ ወይም ትንበያ የሚሰጥበት ሂደት ነው።

ኢንፈረንስ እንዴት እንደሚሰራ ለማስረዳት ባለሙያዎች የኤ. አይን የስራ ሂደት በሁለት ይከፍሉታል። ይህም የመጀመሪያዉ ማሰልጠን (Training) ሲሆን፤ ሞዴሉ ከመረጃዎች እንዲማር የማድረግ ሂደት ወይም ትምህርት ቤት እንደመግባት የሚቆጠር ነው። ሌላው ኢንፈረንስ (Inference) ሲሆን ይህም የተማረውን እውቀት በተግባር ላይ የሚያውልበት ደረጃ ወይም ፈተና እንደመቀመጥ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ።



# ከጎብኚዎች አንደበት . . .



"

ኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት በማቋቋም እና በመጠናቀቅ ላይ ያለውን ከዓለም ሁለተኛውን የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ዩኒቨርሲቲ በመገንባት ወጣቶቿን ለነገው የዓለም ወድድር በማዘጋጀት ረገድ ከአፍሪካ ሀገራት በቀዳሚነት ትገኛለች።

**ዐብይ አሕመድ (ዶ/ር)**
የኢ. ፌ. ዴ. ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር



"

የኤ. አይ ዩኒፖድ የትብብር ውጤት ማሳያ ነው። ይህ የፈጠራ ማዕከል እውን መኾኑ ኢትዮጵያን ከቴክኖሎጂ ጥገኝነት ወደ ቴክኖሎጂ ፈጣሪነት በማሸጋገር ረገድ አዲስ ምዕራፍ የከፈተ ታላቅ እርምጃ ነው።

**ተመስገን ጥሩነህ**
የኢ. ፌ. ዴ. ሪ ምክትል
ጠቅላይ ሚኒስትር



"

የኤ. አይ ዩኒፖድ በቴክኖሎጂዉ መስክ ለተሰማሩ ሁሉም አካላት የተዘጋጀ የአፍሪካን እምቅ አቅም ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚያስችል ማዕከል ነው።

**አሁና ኢዚያኮንዋ**
የተባበሩት መንግሥታት ረዳት ዋና ፀሐፊ እና
የዩ. ኤን. ዲ. ፒ የአፍሪካ ቀጠና ዳይሬክተር



"

በአጭር ጊዜ ተቋቁሞ ከእድሜው በላይ የሆኑ ተግባራትን መከወን ከቻለ ኢንስቲትዩት ጋር መስራታችን ሰፊ ዕድሎች ይከፍታል።

**አስራት አፀደወይን (ዶ/ር)**
የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት



"

ኢንስቲትዩቱ የኤ. አይ ሥነ- ምህዳርን ለማስፋፋት በሚመች መልኩ ተደራጅቶ አግኝተነዋል።

**ዶክተር ዣን ካሴይ**
የአፍሪካ የበሽታ መቆጣጠሪያና መከላከያ
ማዕከል (Africa CDC) ዋና ዳይሬክተር

# ወሩን በፎቶ









በኢትዮጵያ የኳታር አምባሳደር ሳዓድ ሙባረክ አል- ናኢሚ የተመራ ልዑክ በኢንስቲትዩቱ ምልከታ ባደረጉበት ጊዜ





የዳሽን ባንክ የስራ ኃላፊዎች በኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና መስሪያ ቤት በመገኘት የስራ ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት








የሶማሊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ልዑክ ኢንስቲትዩቱን በጎበኙበት ወቅት





የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች የኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩትን በጎበኙበት ወቅት







በኢትዮጵያ የቻይና አምባሳደር ቼን ሃይ የተመራ ልዑካን ቡድን በኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩትን ጉብኝት ሲያደርግ





የአፍሪካ የበሽታ መቆጣጠሪያና መከላከያ ማዕከል (Africa CDC) ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ዣን ካሴይ የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩትን ሲጎበኙ













በጄኔራል ተፋሂ ላይድ የተመራ የአልጄሪያ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች ልዑክ በኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩቱ በመገኘት ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት

# ኢንስቲትዩቱን ይጠይቁ

## እርስዎ ይጠይቁ እኛ እንመልሳለን!

ውድ የዲጂታል ኤ.አይ መጽሔት አንባቢዎች

የሰው ሰራሽ አስተውሎት (ኤ.አይ) ዓለማችንን እየቀየረ ባለበት በዚህ ወቅት በዘርፉ የሚነሱ ጥያቄዎችና የማወቅ ፍላጎቶች ሰፊ መሆናቸው አይካድም። እኛም እርስዎ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ እንፈልጋለን።

“ኢንስቲትዩቱን ይጠይቁ” የተሰኘው ልዩ አምዳችን የተቋሙን የተለያዩ ባለሙያዎች፣ የፖሊሲ አውጪዎችና የቴክኖሎጂ አቅጣጫ ጠቋሚዎች በቀጥታ እንዲያነጋግሩ ዕድል ይፈጥርልዎታል።

contact@aii.et በዚህ የኢሜል አድራሻ ጥያቄዎችዎን ብትልኩልን እኛም መልሱን በቀጣዩ እትማችን ይዘንላችሁ እንቀርባለን።

**ኢንስቲትዩቱን ይጠይቁ! ይሳተፉ! አብረውን ይጓዙ!**
**የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት**

www.aii.et



# የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት


+251 11 558 8786
+251 11 558 5484

40782


**አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ለሁሉም!**
**Artificial Intelligence for All!**